# ልዑል እግዚአብሔር፥

## እንኳን፡ ለ፳፻፲፫ኛው (ሃያ መቶ ዐሥራ ሦስተኛው)
## ጾመ ፍልሰታ ለማርያም፥
## በያለንበት፡ በደኅና አድርሶ፥
## የምስጋና ሱባዔያችንን ለመጀመር አበቃን!

\+ + +

### መግቢያ

እኛ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ በሰማይም፥ በምድርም፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ ላይ በሰፈነችውና የእግዚአብሔርዋ መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ፥ በመላውም ዓለም ተሠራጭተን እየኖርን ባሳለፍነው የሕይወትና የጤንነት ህልውናችን፡ ዓመቱን ሙሉ አቆይቶን፡ እነሆ፡ ከዚህ የምስጋና ሱባዔያችን ለመድረስ አብቅቶናልና፡ እናመስግነው!

ይህችኑ፡ የዘንድሮዋን የፍልሰታ ጾማችንን፡ እንደተለመደው፡ እያንዳንዳችን፡ እንደየዓቅማችን፡ ስለራሳችንና ስለወገናችን፥ ስለአገራችንም ብቻ ሳይኾን፡ ስለዓለሙ ኹሉ ደኅንነት ጭምር፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሰንና በሱባዔ ተጠምደን፡ በምናካኺደው የምስጋና ጾም-ጸሎታችን የምንፈጽማት፡ በአዲሱ መለኮታዊ የዐዋጅ ቃል መንፈስና ዘመን ይኾናል።

**በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የተስተካከለውና የተሟላው ሥርዓተ-ጸሎታችን፡ ተጠናቅቆ እስኪቀርብልን ድረስ፡ ይኸው የምስጋና ጾም-ጸሎት ሱባዔያችን፡ ከዚህ በፊት፡ ለበዓለ ኢትዮጵያ ተዘጋጅቶልን የተገለገልንበትን፡ ያንኑ የ፳፻፲፬ ዓ.ም. ጸሎት፣ ሥርዓትና መመሪያ የተከተለ ይኾናል። ይህንም፡ የጸሎት ሥርዓትና መመሪያ፡ በዚሁ የኀዋ ሰሌዳ ላይ፡ "ቤተ መዛግብት" በሚለው ክፍል ውስጥ፡ እናገኘዋለንና፡ ያን ከፍተን፡ በመመልከት፥ ዐትመንም በማውጣት፡ ልንጠቀምበት ይቻለናል።

ይህች፡ የጾመ ፍልሰታ ሱባዔ፡ በኢትዮጵያ ምድር ለምንኖረው፡ በዝናቡ የክረምት ወራት፥ በቀሩትም፡ የየክፍለ ዓለማቱ አህጉራት፡ ተበትነን ለምንገኘውም፡ እንደየወራቱ የአየራቱ ጠባያት፡ ከሚፈጸሙትና ትዝ ከሚሉን ባህሎቻችን መካከል፡ ቀዳሚዋና ዋናዋ ኾና ትገኛለች።

በእርሷም፡ ካህናት፥ ትላልቆች ወንዶችና ሴቶች ምእመናንና ምእመናት፥ ብላቴኖችና ልጆች ብቻ ሳይኾኑ፡ ሕፃናት ጭምር እየጾሙ፥ እያስቀደሱና እየቆረቡ፡ የኹለት ሳምንት፡ የሱባዔ ጊዜያቸውን፡ በቤተ ክርስቲያንና በየቤታቸው ያሳልፋሉ።

በጾመ ፍልሰታ ሰሞን፡ የእግዝእተብሔራችንና የመድኃኒታችን፣ የሃይማኖታችንና የአገራችን፥ የእናታችንና የንግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ዜና ፅንሰቷና ልደቷ፥ ሕይወቷና ዘለዓለማዊነቷ፥ በአጠቃላይ፡ መለኮታዊው እና ትስብእታዊው ማንነቷ፥ እንዲሁም፡ በምሥዋ'ዐ-መድኃኒትነቷ፡ ፍጥረታተ-ዓለማቱን ያዳነችበት፣ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡ እርሷን ምክንያት አድርጎ፡ በቤዛ ሰላመ-መስቀሉ፡ ራሱን፡ ለፍጥረቱ የገለጸበትና ዘለዓለማዊዉን ሰላም ያስገኘበት፡ የሥጋዌው፡ ማለትም፡ ሰው የኾነበት ምስጢር ኹሉ፡ ተብራርቶ ይነገርበታል። ቅዱሳንና ቅዱሳት ሓዋርያት፡ ይህን ሱባዔ፡ ለምን እንደጀመሩት፥ በዓመቱም፡ እንዴት እንደቀጠሉት፡ ዜና መዋዕሉ ይታወስበታል።

## ለመኾኑ፡ "ሱባዔ"፥ "ሱባዔ መግባትስ" ምንድር ነው?

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዓመቱ ውስጥ፡ ጠብቀን ከምንፈጽማቸው ጾሞቻችን መካከል፡ "ጾመ ፍልሰታ" አንዷ ናት። እርሷንም፡ ለኹለት ሳምንታት፡ በሚዘልቅ ሱባዔ፡ ከነሓሴ ፩ እስከ፲፭ ቀን ድረስ እንዘክራታለን። በተከታታይነት የሚቀጥሉት፡ ኹለቱ ቀኖች፡ ማለትም፡ ነሓሴ ፲፭ እና ፲፮፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ፍልሰታዋን፡ ማለትም፡ ከምድር ወደሰማይ የኼደችበትን መለኮታዊ ትንግርት በማዘከር፡ የፍልሰታ በዓሏ የሚከበርባቸው ዕለታት ናቸው።

እዚህ ላይ፡ በሃይማኖት ሊታወቅና በምግባር ሊገለጽ የሚገባው፡ አንድ መለኮታዊ እውነታ አለ፤ ይኸውም፡- **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** እምነትና ሥርዓት፡ **እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም፡ ሕያው ፍልሰት እንጂ፡** እንደልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሞትና ትንሣኤ የሌለባት፥ ያላገኛትም መኾኗ ነው።

ታዲያ! በቀደመ ነገር፡ "ሱባዔ" እና "ሱባዔ መግባት" ምን ማለት እንደኾነ ማወቁና መረዳቱ፡ አግባብና አስፈላጊ ስለሚኾን፡ እስኪ፡ ስለእነዚሁ ቃላት ቍም ነገርነት፡ ለመግቢያ ያህል፡ ጥቂት እንበል!

"**ሱባዔ**"፡ "ሰብዖ" = "ሰባት ማድረግ" ከሚለው የግእዝ ዘር ረብቶ የወጣ ነው። የኢትዮጵያ ልጆች፡ በቅመራ፡ ከሰባቱ የእግዚአብሔር የሥነ ፍጥረት ቀኖች ያገኙት፥ ከዚሁ እውነታ የተነሣም፡"ፍጹም ቍጥር" ብለው የሰየሙት፥ ይህንኑም፡ ለሌሎች፣ ለሴማውያን ሕዝቦች፥ ለዕብራውያን ጭምር ያሳወቁት ቃል ነው። ቃሉም፡ በሰባትነት ቍጥር፥ ወይም፡ ብዛት ለሚወሰኑ ጊዜያትና ዕለታት፥ ዓመታትና ዘመናት ይውላል።

ስለዚህ፡ ከእሑድ እስከ ሰንበት ያሉት፡ ሰባት ዕለቶች፡ አንድ ሱባዔ ናቸው። ሰንበት የሚለው ቃል፡ ራሱ፡ ከዚሁ የቃል ዘር፡ ረብቶ የተገኘ መኾኑን፥ የፍልሰታ ጾምም፡ ፲፬ ዕለታትን የያዘ በመኾኑ፡ ኹለት ሱባዔዎች መኾኑን ያስተውሏል።

"**ሱባዔ መግባት**" ማለት ደግሞ፡ በእነዚህ፡ ሰባት፥ ወይም፡ ዐሥራ-አራት ዕለታት ውስጥ፡ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዝእተብሔር እም፥ ከእግዚአብሔር ወልድና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር፥ በተለይም፡ እኒህ ኹሉ፡ የአንዱ ፈጣሪ፥ የአንዱ አምላክ መገለጫዎች የኾኑት አካላትና ባሕርያት፡ በፍጹም ተዋሕዶ አንድ ከኾኑባት፥ **ራሷም፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከኾነችው፥** ደግሞም፡ የፈጣሪ ዕፁብ ድንቅ የኾኑት፡ የጥበብና የትንግርት ሥራዎች ከተከሠቱባት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፥ ከሥነ ፍጥረትም ጋር ሳይቀር፡ በይበልጥ፡ በእውነት እና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ መገናኘትና መነጋገር ነው።

በዚህን ጊዜም፡

የነፍስ የኾነውን፡ **ጾምን**፡ ማለትም፡ የውስጥ አስተሳሰብን፡ ከክፉት ኹሉ፡ በእውነተኛ ንስሓ አንጽቶ፡ ወደመልካምነት መመለስን በማስቀደም፥

የሥጋ የኾነውን፡ **ምጽዋትን**፡ ማለትም፡ በጤናማ የፍቅር ስሜት ኾኖ፡ ለፍጡር ኹሉ፡ የደግነትና የበጎ ምግባርን ለመፈጸም፡ ራስን፡ በውስጥ አስተሳሰብ ሳይቀር፡ ማዘጋጀትን በማስከተል፥

የመንፈስ የኾነውንም፡ **ጸሎትን**፡ ማለትም፡ *ለልመና እና/ወይም፡ "እንዲህ፡ ይደረግልኝ!" ብሎ ለመጠየቅ ሳይኾን፡* እርሱ፡ ቸር ፈጣሪ፡ ሳይጠየቅ ስላደረገው፡ ስለተትረፈረፈውና ስለማይቋረጠው፥ እየጨመረ ስለሚኼደውም፡ የተፈጥሮና አምላካዊ ጸጋው፣ ይኸውም፡ በልዩ ቸርነቱና ልግሥናው ስላደረጋቸው ስጦታዎቹ ኹሉ፡ በባለውለተኛነትና በአመስጋኝነት፥ በልጅነት የመውደድና የማክበርም ስሜት በመኾን፡ መለኮታዊዉን በረከት ለመቀበል ጭምር፡ ከእግዚአብሔርና የእርሱ ከኾኑት መሰሎቹ ጋር፡ በፍጹሙ እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ አምልኮና የተመስጦ ህልውናም ኾኖ፡ በቀጥታ፡ በአሳብ፥ በኅሊና፥ በመንፈስ ተገናኝቶ መነጋገርን ማካተቻ በማድረግ፥

በራስ በኩል ከሚቀርበው ጸሎት በቀር፡ ሌላ ማከል ቢያስፈልግ እንኳ፡ አግባብነት ያላቸውን መጻሕፍትን በመመልከትና በማንበብ፥ በቃልም፡ ጸሎታትን በመድገም፡ በይበልጥ ግን፡ በእግዚአብሔር እውነት እና ቅዱስ በኾነው መንፈስ በመገናኘትና በመነጋገር፡ ሊያካኺዷቸውና ሊፈጽሟቸው ይገባል።

እነዚህን፡ የሱባዔ ሃይማኖታውያት ምግባራት፡ በግል መኖሪያ ቤት፥ ወይም፡ በአንድ ቦታ ተወስኖና ከሰው ተለይቶ፡ ተኝቶም፡ ተጋድሞም፥ ተነሥቶም፥ ቆሞም፡ ተቀምጦም፥ እየተንቀሳቀሱም፥ እየኼዱም፥ እየሠሩም፥ እየተመገቡም፥ እየታጠቡም፥ እየተጸዳዱም እንኳ፡ ለማካኼድና ለመፈጸም ስለሚቻል፡ በጋራ የጸሎት ቤት መገኘትን፡ ይህን ያህል፡ አስፈላጊ አያደርገውም።

# ስለዘንድሮዋ የፍልሰታ ሱባዔያችን።

፩ኛ. ባለፈው ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት፥ በነሓሴ ፲፯ ቀን፥ "ቍጥር ፩/፳፻፰ ዓ. ም. ቃለ ዐዋድ! እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር!" ማለትም፡ "የዐዋጅ ቃል! ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ በሚል አርእስት በተዘጋጀው፡ በታላቁ መለኮታዊ ቀዳሚ መልእክት መግቢያነት፡ ሰብአዊዉን ዘር ለሚያካትተው፡ ለመላው ፍጥረተ-ዓለም፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ በተመሠረተ፡ የይፋ ጽሑፍ፡ የታወጀበትን፡ ሰባተኛውን ዓመት፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም፡ ከ"ቍጥር ፪/፳፻፰ ዓ.ም." እስከ"ቍጥር ፲፱/፳፻፱ ዓ.ም." እየተባሉ፡ በተከታታይ ይፋ የወጡትን የእግዚአብሔር መንግሥት ዐዋጆች፡ እያስታወስንና እያሰብን ስለምናከብራት፡ **የዘንድሮዋን የፍልሰታ ሱባዔያችንን፡ የተለየች እናደርጋታለን።**

፪ኛ. በአኹኑ ጊዜ፡ በአገራችንና በመላው ዓለም፥ በየአህጉሩም፡ በከፍተኛና በሚያሠቅቅ መልክና ይዘት፡ እየተካኼደ ያለው፡ ረቂቁና ግዙፉ ሰይጣናዊ ችግር፥ ወረርሽኝ፥ የእርስ በርስ ደም መፋሰሱንና ዕልቂቱን ጨምሮ፡ እጅግ አሳሳቢ ከኾነ ደረጃ እንደደረሰ ይታያል። ይህን፡ በፍጡራን ዘንድ፡ ምንም ዓይነት መፍትሔ ሊገኝለት ያልተቻለውን፥ ሰብአዊዉንም ተስፋ ያስቈረጠውን አሳዛኝ ኹኔታ፡ ከመጨረሻው የጥፋት ፍጻሜ ማዳን፡ ዓቅሙና ክሂሎቱ ያለው፡ የመለኮታዊው ቸርነትና ኃይል ባለቤት በኾነችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ ብቻ እንደኾነም ይታወቃል።

ስለዚህ፡ በዚች ሱባዔያችን አማካይነት፡ ይህን እግዚአብሔራዊ እውነታ፥ ደግሞም፡ የነገሮች ኹሉ፥ የፍጡሮቻቸውና የፍጥረታቸውም ኹሉ ባለቤቶችና ወሳኞች፡ በቸርነታቸውና በቤዛነታቸው፡ ክፉውን ኹሉ አሸንፈው ያስወገዱት፡ እናቲቱ እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና ተወዳጁ ልጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እንጂ፡ ዲያብሎሳዊው የጥፋቱ ጠንቅ አለመኾኑን፡ ጠለቅ ብለን፡ በበለጠ ተመሥጦ፡ የምናውቅና የምንረዳ፥ የምንገነዘብና የምናምን እንኾናለን።

ከዚህ የተነሣ፡ በዚህ የዕውቀታችንና የመረጃችን፥ የግንዛቤያችንና የእምነታችን መንፈስ ቅዱሳዊ ኃይል ተጠቅመን፡ ይህን፡ የኖኅን፥ የሰዶምንና የገሞራን ዘመናት የመሰለውን፥ ለራሱ መጥፊያ በሠራው እሳት፡ ተቃጥሎና ነድዶ ሊደመሰስ እየተጣደፈ ያለውንም ዓለም፡ እያንዣበበበት ካለው የመቅሠፍት ደመና፡ በእውነተኛ ንስሓው ለማትረፍ ይቻለናል።

እንግዴህ፡ በዚህ ሃይማኖታዊ ምግባራችን መልካም ፍሬ ምክንያት ነው፡ የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት ጭምር፡ ከእኛ ጋር ዐብረውን ኾነው፡ የደስታ ምስጋናችንን፡ በታላቅ ይባቤ በመዘመር፥ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ዙፋኑ በኾነችው፡ በእርሷ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ለተቀመጠው ቸሩ ፈጣሪያችን፡ በፍጹም ሓሤት የምናቀርብባትን፡ የዘንድሮዋን የፍልሰታ ሱባዔያችንን፡ የተለየች የምናደርጋት።

## የድንግል ማርያም፡
## የማንነቷ ዝክረ ነገር ባጭሩ።

ለመኾኑ፡ ድንግል ማርያም፡ ማን ናት? ለሰብኣዊው ፍጡር፡ ስለእርሷ ማንነት ለመናገር፥ ወይም፡ ለመጻፍ፡ የሚቻለው፡ ማንም እንደሌለ፡ በእርግጠኝነት መመስከር፡ ለእውነተኞች ሰዎች፡ ከቶ አያዳግታቸውም። ስለዚህ፡ ለዚህ ጥያቄ፡ በቂ የኾነ የተሟላ ምላሽን ለመስጠት፡ እንኳንስ ሊያደርጉት፡ ሊታሰብም ስለማይቻል፡ እንዲያው፡ ዓቅማችን የፈቀደውን ያህል፡ ያውም፡ በእግዚአብሔር እውነት እና በመንፈስ-ቅዱስ አምልኳችን ኾነን፡ እጅግ በጥቂቱ እናቀርብላችኋለን፡-

፩. "<u>ድንግል"፡ ስለሚለው ቃል</u>፡- ኹሉን የፈጠረውና የያዘው እግዚአብሔር፡ ጥንት በሌለው አንድ አምላክነት፡ በራሱ ህልው ኾኖ ሲኖር ሳለ፡ ዓለማትን፡ ዛሬ ባሉበት መልክና ይዘት ለመፍጠር ባሰበ ጊዜ፡ መጀመሪያ፡ ጾታ-አልባ የኾነ፡ አንድ ራሱን፡ እኩል፡ ለኹለት ከፈለ፤ አንድ ወገኑ፡ በወንድነት ጾታ፡ እግዚአብሔር አብ ኾኖ፡ "ድንግሉ ሙሽራ፡ [ባል]" ሲባል፣ አንዲቱ ወገኑም፡ በሴትነት ጾታዋ፡ እግዝእተብሔር እም ኾና፣ "ድንግሊቷ ሙሽሪት፡ [ሚስት]" ተባለች። ስለዚህ፡ ይህ፡ "**ድንግል**"፡ የሚለው ቃል፡ የእግዚአብሔር አብ እንደመኾኑ ኹሉ፡ እንዲሁም፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፥ ዓለም ከተፈጠረ በኋላም፡ እርሷ ለተዋሓደቻትና እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት ለወለደችው፡ ለቅድስት ማርያምም፡ የተሰጠ፡ ዘለዓለማዊ የማዕርግ ስም ነው።

አዎን! መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ እርሷ ሙሽሪቱ ድንግል እግዝእተብሔር እም፡** ለእርሱ፡ ለሙሽራዋ ድንግል፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ አንድዬ የበኵር ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመጀመሪያ፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ በመለኮትነት፥ ዓለም ከተፈጠረ በኋላም፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ በቅድሚያ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ድንግል ማርያምን፡ ተዋሕዳ፡ በሰውነት የወለደችለት ናት።

ይኸውም፡ ልጇን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከአባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በሰውነት በወለደች ጊዜ፡ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው ነው፡-

**"ወዝ ኵሉ ዘኮነ፡ ከመ ይትፈጸም፡ ዘተብህለ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፡ በነቢይ፡ እንዘ ይብል፡- 'ናሁ፡ <u>ድንግል</u> ትፀንስ፤ ወትወልድ ወልደ፤ ወይሰመይ ስሙ ‹አማኑኤል!›፤ ዘበትርጓሜሁ፡ ‹እግዚአብሔር ምስሌነ!›'"**

ማለትም፡ "ይህ ኹሉ የኾነው፡ በነቢይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ 'እነሆ! <u>ድንግል</u> ትፀንሳለች! ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ ስሙም፡ ‹እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋራ ነው!› የሚል ትርጉም ያለው፡ ‹አማኑኤል!› ይባላል!' የተባለው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።"

ይህችው፡ ድንግል ማርያም፡ በመለኮትነቷና በሰውነቷ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የኾነው፡ ይህ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ፡ ፍጹምና ምሉእ ነው።

ከጥንት ጀምሮ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሥይምተ እግዚአብሔር ኾነው፡ በአጼዩትነት የሚቀቡት ኢትዮጵያውያት ንግሥቶች፡ ምንጊዜም ደናግል የሚኾኑት፡ ይኸው ትንቢት፡ "ምናልባት፡ በአንዳቸው ሰውነት፡ ሊደርስና ሊፈጸም ይችል ይኾናል!" ከሚለው፡ ከዚህ የዝግጅት ብቅዓት የተነሣ መኾኑን፡ እዚህ ላይ ማጤን ይገባል።

ይህም፡ ከባለቃል ኪዳኑ እስራኤላዊ ንጉሥ ዳዊትና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ቤትሳባ ከተወለደው፡ ከንጉሥ ሰሎሞን አብራክ፡ የበኵር ልጁን፡ ንጉሥ ምኒልክን፡ በድንግልና እንደወለደችው፥ "ንግሥተ አዜብ" ወይም፡ "የደቡብ ንግሥት"፥ "ንግሥተ ሳባ"፥ ወይም፡ የሳባ ንግሥት" በሚል ስያሜ እንደምትታወቀው፡ እንደአጼዩት ማክዳ ማለት ነው። (ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫፤ ፲፪፥ ፵፪።)

፪. "**ማርያም**"፡ **ስለሚለው ስያሜ**፡- "**ማርያም**" ስለሚለው ስም፡ ጥቂት እንበል! በግእዝ፥ በኢትዮጵያኛ ጭምር፡ "ስምን መልአክ ያወጣዋል!" የሚለው ዘይቤ ሳይዘነጋ፡ ስም፡ ለአንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ለወንድ ኾነ፡ ለሴት፥ የሚሰጠው፡ እንዲያው፡ ያለምክንያትና ያለትርጉም፡ ዝም ብሎ፡ በከንቱ አይደለም።

ስለዚህ፡ "'**ማርያም**' የሚለው ስም፡ '**እመ አርያም**'፡ ማለትም፡ 'በአርያም'፥ ወይም፡ 'በሰማያት ያለች'፥ ወይም፡ 'የምትኖር እናት'፤ ደግሞም፡ '**እምአርያም**'፡ ማለትም፡ 'ከአርያም'፥ ወይም፡ 'ከሰማያት የኾነች'፥ ወይም፡ 'ከሰማያት'፥ ወይም፡ 'ከአርያም የተገኘች' ማለት ነው!" ተብሎ ይተረጐማል።

፫. "**እግዝእተብሔር እም**"፡ **ስለሚለው አጠራር፡ በበለጠ ለማብራራት**፡- ይህች ድንግል ማርያም፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ "እግዝእተብሔር እም"፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር እኩያ የኾነች፡ "እናቲቱ እግዚአብሔር" ለመኾን የበቃች ናት።

"ይህ፡ እንደምንድር ነው?" ቢሉ፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" በተባሉት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ያለው መልስ፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ይገለጻል፡-

፬. **ስለእግዚአብሔር አንድነት፥ ኹለትነትና ሦስትነት ምስጢር፡-** ጥንት በሌለው መጀመሪያ፡ የዓለማቱና የፍጥረታቱ አስገኚና ሠሪ የኾነው እግዚአብሔር፥ እርሱም፡ አንድ አምላክ የመኾኑን እውነታ ሊያረጋግጥ፡ ስሙ፡ "እነ"፡ ማለትም፡ "እኔ" መኾኑን፡ ኋላ፡ ራሱንና ስሙን፡ በኹለቱ አሌፋት ለፍጥረቱ ያሳወቀውና በዚሁ ስም የተጠራው ፈጣሪ፡ አንድ ልጅን ወልዶ፡ ረቂቃንና ግዙፋት ዓለማትንና ፍጥረታትን ለመፍጠር ባሰበ ጊዜ፡ በቅድሚያ ያደረገው መለኮታዊ ትንግርት ምን እንደኾነ እንመልከት!

ስሙ፡ በግእዙ፡ "**አነ**"፥ ወይም፡ በኢትዮጵያኛው፡ "**እኔ**" በሚል፡ **በአንድ ቃልና በኹለት አሌፋት የተገለጸው፥ የታወቀውም ፈጣሪ፡** አንድ ራሱን፡ "**አ**" በሚለው፡ በአሌፋቱ ቀዳሚ ፊደል፡ ጥንተ-አንድነቱን ካመላከተ በኋላ፡ "ኹለት ነኝ" በማለት፡ ኹለትነቱን ለማሳየት ደግሞ፡ ይህችኑ፡ "**አ**"ን፡ በኹለት ሰባት፥ ወይም፡ በኹለት ሱባዔ፡ ከምትቈጠረው፡ የአሌፋቱ ፲፩ኛ ከኾነችው፡ ከ"**ነ**" ጋር በማዋሓድ፡ አንድነቱንና በተዋሕዶ ወደአንድነቱ የተመለሰው ኹለትነቱ የተገለጠበትን፡ ራሱን፡ "**አነ**" በሚለው፡ ጾታ-አልባ ስሙ አረጋገጠ። "አነ እግዚአብሔር" በማለቱ።

ደግሞም፡ የአሌፋቱ ቀዳሚ ፊደል በኾነው፡ በ"**አ**" የመጀመሪያ ፊደል፡ "**<u>አ</u>ነ ውእቱ አልፋ ወኦ!** መጀመሪያውም፡ መጨረሻውም፡ እኔ ነኝ!" ያለውን ለማጽናት፡ "**<u>አ</u>ቡነ!** ፣ <u>አ</u>ባታችን!" አሰኘ። አኹንም እንደገና፡ "**አ<u>ነ</u> ውእቱ አልፋ ወኦ!** መጀመሪያውም፡ መጨረሻውም፡ እኔ ነኝ!" ያለውን ለማጽናት፡ "**እም<u>ነ</u>**! እናታችን!" አሰኘ። "እግዚአብሔር አብ" እና "እግዝእተብሔር እም" በማሰኘቱ።

ስሙ፡ እንዲህ፡ አንድነቱን በሚያመላክተው፡ "**አነ**" በሚለው፡ በአንዱ ቃልና ኹለትነቱን፥ ደግሞም መጀመሪያውና መጨረሻው፡ እርሱ መኾኑን በሚያመላክቱት፡ "**አ**" እና "**ነ**" በተባሉት፡ በኹለቱ አሌፋት አሳወቀ።

እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ ለብቻው፡ አንድ በመኾኑ፡ "**አነ**" ማለትም፡ "እኔ" የሚለውን ስም፡ ለራሱ መስጠቱና ዐሥርቱ (ዓሥሩ) ቃላት የተቀረጹባትን ጽላተ ኪዳን በያዘችው ታቦተ ጽዮን ላይ ራሱን መግለጡ፡ ከላይ በተሰጠው ሓተታ ተብራርቷል።

በዚችው፡ በታቦተ ጽዮን ውስጥ ለታቀፉት፡ ለዐሥሩ ቃላት፡ በአንድ በኩል፡ በግእዙ አኀዝ፡ ዐሠርት (ዓሥር) ለሚለው ቍጥር፡ መለያና መታወቂያ ኾና የተመደበችው ምልክት፡ እንዲህ፡ ዕዝል ቅጥል የሌላት፡ ይህች ዓይነቷ "፲" አንዲት ቅንጣት ሠረዝ መኾኗ፡ የቀደመ አንድነቱን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፡ በእነዚያ፡ በዐሥሩ ቃላት ውስጥ፡ ራሱን፡ ኹለት ጊዜያት ብቻ፡ "**አነ፥ እኔ**" ማለቱ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር አብ እና በእግዝእተብሔር እም፡ ተከታይ ኹለትነቱን፡ አረጋግጦ ማሳየቱን ያመለክታል።

እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ በሌለው ጥንት፡ ራሱን፡ "**አነ**! እኔ!" እያለ፡ <u>**በአንድነቱ**</u> በሚጠራበት፡ በዚያ፡ በመለኮታዊው፥ ጾታ-አልባና የብቸኝነት ስሙ እየኖረ ሣለ፡ ኋላ ደግሞ፡ ራሱን፡ "**ንሕነ**! እኛ!" ብሎ በመጥራት፡ አስቀድሞ፡ "በእግዚአብሔር አብ"ነቱ እና በ"እግዝእተብሔር እም"ነቷ፡ ኹለትነቱን፥ ከዚያ አያይዞም፡ "**ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሐደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ፤ ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፤ ሰብእ ኢይፍልጥ!**

"ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ። ከእንግዲህም፡ ኹለት አይደሉም፤ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ። እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!" ብሎ፡ በፍጥረት ጊዜ፡ ለአዳምና ለሔዋን፡ ባገዘፈው፡ የባልና ሚስት ሥርዓት፥ በመጨረሻም፡ "እግዚአብሔር አብወእም፤ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ!" ብሎ፡ ሥላሴነቱ ወደተከሠተበት፡ ወደሦስተኛው ደረጃ መለኮታዊ ትንግርት፡ ራሱን አሸጋግሮ፡ ከፍ በማድረጉ፡ ማንነቱን፡ የበለጠ ገለጠ፤ አሳወቀ። (ዘልደት[ዘፍጥ.] ፩፥ ፳፯፤ ፪፥ ፳፬። ዘጸአ. ፫፥ ፲፫-፲፬። ማቴ. ፲፱፥ ፬-፯።)

ይኸውም፡ **የአንዱ** እግዚአብሔር፡ **ኹለትነቱ** የተከሠተበት፡ አንዱ እውነታ፡ ከላይ እንደተወሳው፡ ይኸው፡ **አንዱ** እግዚአብሔር፡ በአንደኛው እኩሌታ ወገኑ፡ "**እግዚአብሔር አብ**" ተብሎ፡ በወንድነትና በድንግልና ሙሽርነት፥ በባልነትና በአባትነት፥ በሊቀ-ካህናትነትና በንጉሠ-ነገሥትነት፤ በኹለተኛው እኩሌታ ወገኑ ደግሞ፡ "**እግዝእተብሔር እም**" ተብላ፡ በሴትነትና በድንግልና ሙሽሪትነት፥ በሚስትነትና በእናትነት፥ በመቅደሰ-ክህነትነትና በንግሥትነት፡ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፡ አንድያ ልጃቸው የኾነውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመለኮትነት መውለዳቸው ነው።

እርሱ፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ ረቂቃኑንና ግዙፋኑን ዓለማታቸውንና ፍጡሮቻቸውን፡ የማስገኘቱንና የማከናወኑን፥ የማስተዳደሩንና የመጠበቁን መለኮታዊ ሥልጣንና ኃይል የያዘው፡ የቅድስት ሥላሴ፡ አንዱ አካላዊውና ባሕርያዊው ቃል መኾኑን ማስተዋል ነው።

ይህ መለኮታዊ ልደት፡ የኾነውና የተፈጸመው፡ **እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም፡ ኹለቱም፡ በቀደመው የአንድነት ህልውናቸው ሳሉ፡ በሠሩትና በመሠረቱት፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓታቸው አማካይነት መኾኑ፡** መታወቅ አለበት።

የአንዱ እግዚአብሔር፡ **ሥላሴነቱ [ሦስትነቱ]** የተከሠተበት፡ ሌላው እውነታ ደግሞ፡ **እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም**፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር የመጣው ፍጥረት ኹሉ፡ መንፈሳዊው ኾነ፤ ሥጋዊው፡ ሕያው ኾኖ፡ ህልውናው፡ በመለኮታዊዎቹ ፍጹም ሕይወትና እውነት፥ ሰላምና ፍቅር፥ ሥርዓትና ጸጥታ፥ ቅንነትና በጎነት ጸንቶ፡ ለዘለዓለም እንዲቀጥል ያደርግ ዘንድ፡ መለኮታዊዉን ሥልጣንና ኃይል የያዘውን፥ የቅድስት ሥላሴ፡ አንዱ አካልና ባሕርይ የኾነውንም፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፡ ከራሳቸው አንድነት፡ ማሥረፃቸው ነው።

**አንዱ** እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ **በሦስትነት** በተገለጸበት መለኮታዊ ህልውናው፡ "**ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!**" ተብሎ በሚመሰገንበት ሥላሴነቱ፡ አንደኛው **ቅድስና**፡ በአንድነት፡ የእግዚአብሔር አብወእም ሲኾን፥ ኹለተኛውና ሦስተኛው ቅድስናዎች ደግሞ፡ በየተራቸው፡ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መኾናቸው፥ በተለይም፡ የመጀመሪያው ቅድስና፡ በአንድነት የተገኘበትን፡ **የእግዚአብሔር አብን እና የእግዝእተብሔር እምን፡ የፍጹም አንድነት ህልውና የሚያሳይ** መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

ይህም፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት መሠረት፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሲሕ፡ የባልና የሚስት አንድነትን በሚመለከት፡ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጸውን፡ የጥንቱን፡ የሥነ ፍጥረቱን ሥርዓት ጠቅሶ ሲናገር፡ "**ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር እምትካት፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ። ...ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሐደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ።**

"ጥንቱኑ፡ የፈጠራቸው እግዚአብሔር፡ ወንድና ሴት አድርጎ ሠራቸው። ...ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ። እንግዴህ፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም። እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!" ከሚለው፣ ከላይ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው መለኮታዊ ቃል ጋር፡ እንዴትና የቱን ያህል እንደሚስማማ፡ ልብ ማድረግ ነው። (ማቴ. ፲፱፥ ፬-፮።)

**፫. "አምላክ ሰው ኾነ! ሰው አምላክ ኾነ!"** ስለሚለው ዘይቤ፡- "**ወይቤ እግዚአብሔር፡- 'ንግበር ሰብአ፡ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ፡ ከመ ይኰንን ...ኵሎ ምድረ፤ ወኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር። ...ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ እመሕያው፡ በአምሳለ እግዚአብሔር፤ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ። ወባረኮሙ እግዚአብሔር፤ ወይቤሎሙ፡- 'ብዝኁ ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ!'**

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'ሰውን፡ በመልካችን፥ እንደምሳሌያችን እንፍጠር! ...ምድርን ኹሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውንም ኹሉ ይገዛ ዘንድ! ...እግዚአብሔርም፡ የሕያዋንን እናት ልጅ፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- 'ብዙ! ተባዙም! ምድርንም ምሏት! ግዟትም!'"

ደግሞም፡ "**ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ፣ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ!**

"እነሆ፡ አዳም፡ መልካሙንና ክፉውን በማወቅ፡ ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፰። ፪፥ ፳-፳፬።)

ከዚህ በላይ በተሰጠው፥ ከዚህም በታች፡ በሚሰጠው ሐተታ፥ በተጠቀሱትና በሚጠቀሱትም፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት መሠረት፡ በጽላተ-ሙሴም ኾነ፡ በትስብእት ሥጋዌ አማካይነት፡ ከልጇ ከወዳጇ፡ ከወልደ-እግዚአብሔር ኢየሱስ መሲሕ በፊት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ በቅድሚያ፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ የተዋሐደችው፡ "እግዝእተብሔር እም" መኾኗን፡ በማስተዋል መመልከቱ፡ በእጅጉ ያስፈልጋል። ከዚህ የተነሣ ነው፡ እግዝእተብሔር እም፡ የሰብኣዊቷን፡ የድንግል ማርያምን ፍጹም ሰውነት በተዋሐደች ጊዜ፡ "**ቃል፡ ሥጋ ኮነ!** አምላክ ሰው ኾነ!" ተብሎ የተነገረውና የተጻፈው መለኮታዊ ቃል፡ እውን ኾኖ መፈጸሙ የተረጋገጠው። (ዮሐ. ፩፥ ፲፬።)

፮. "**ኢትዮጵያ**"፡ ስለሚለው የስያሜ ቃል፡- "የእግዚአብሔር ልጅና ካህን፥ የእውነትና የሰላምም ንጉሥ" በተባለው፥ በመጠሪያ ስሙም፡ "ኢትዮጲስ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ "**ኢትዮጵያ**" የተባለችውና መላውን ሰብኣዊ ፍጥረት አጠቃልላ የያዘችው፣ በፈጣሪው በእግዚአብሔርም ዘንድ፡ ፍጥረትን የምትወክለው ሴት፡ ከዚችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በስተቀር፡ ሌላ ማን ሊኾንና ሊኖር ይችላል? ሊኾንና ሊኖር የሚችል፡ ሌላ ማንም ፍጡር፥ ወይም፡ ነገር፡ ከቶ የለም።

ይህን፡ እግዚአብሔራዊ እውነታም፡ "**ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!** ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!"፥

ደግሞም፡ "'**አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።** ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" በሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ተረጋግጦ ይታወቃል። (መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፫። አሞ. ፱፥ ፯።)

፯. ስለታቦተ-ጽዮን፡- ራሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ኢትዮጵያዊነት ተወልዶ፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት የመጣው፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን በማፍረስ፡ በሓሰት፡ "የአብርሃም፥ የይስሓቅና የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉትን፥ እንዲያውም፡ በእርሱው አንደበት፡ "**አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ!**

"እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ!" ያላቸውን፥ አኹንም፡ ጽዋቸው ሞልቶ እየፈሰሰ ባለው ኃጢኣታቸው ምክንያት፡ ፈጽመው ሊጠፉ ያሉትን፡ አይሁድን ለማዳን መኾኑን በመግለጽ፡ ለተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል፡ እንዲህ ይላል፡-

"**ውስተ ፍኖተ አሕዛብ፡ ኢትሑሩ! ወሀገረ ሳምር፡ ኢትባኡ! ወሑሩ ባሕቱ፡ ኀበ አባግዕ ዘተሓጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል።** ወደአሕዛብ መንገድ አትኺዱ! ወደሳምራውያን አገርም፡ አትግቡ! ነገር ግን፡ ከእስራኤል ወገን ወደጠፉት በጎች ኺዱ!"

ቀጥሎም፡ "**ኢተፈነውኩ፡ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ፡ ዘተሓጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል!** "ከእስራኤል ወገን ወደኾኑ፡ ወደጠፉት በጎች ብቻ እንጂ፡ ወደሌላ አልተላክሁም።" (ማቴ. ፲፥ ፭-፮፤ ፲፭፥ ፳፬። ዮሐ. ፰፥ ፵፬።)

እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚህ፡ መለኮታዊ ማንነቱና ኢትዮጵያዊ ምንነቱ፡ እንዲህ በሚል፡ ግልጽና ቍርጥ ቃል ያሳወቀውን፥ ደግሞም፡ በእነዚሁ አይሁድ፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የክፋት ኃጢኣት ምክንያት፡ በጣዖት መልክ እስከመገለጽ ያደረሰውን፡ ይህን ታላቁን ተልእኮውን ሊፈጽም፡ ገና፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን፡ በእግዚአብሔር ቃልነቱ፡ ዐሠርቱ ቃላትን ኾኖ፡ በግዑዝ ግዝፈት፡ ወደዚህ ዓለም መጣ።

*የእግዚአብሔር ቃል የኾነው፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ እንዲህ፡ ዐሥርቱ ቃላትን ኾኖ፡ በኹለቱ የድንጋይ ጽላት (ሰሌዳዎች) ላይ፡ በእግዚአብሔር አብ እጅ በተያዘው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብርዕ (ብዕር) ይጻፍ ዘንድ፡* ***እግዝእተብሔር እም፡*** *ፈቃዷ ኾኖ፡ "ታቦተ ጽዮን፥ ጽላተ ኪዳን" በተባሉት፡ በእነዚሁ፡ ኹለት የድንጋይ ጽላት (ሰሌዳዎች) ላይ፡ በቅድሚያ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ መዋሐድ ስላስፈለጋት፡ እነሆ! ይኼ መለኮታዊ ትንግርት ተፈጽሞ፡ ይህችው፡ "ታቦተ ጽዮን፥ ጽላተ ኪዳን" አምልኮአዊ ተልእኮዋን፡ በምድር ላይ ማካኼድና ማከናወን ጀመረች።*

*እኒህ፡ ዐሥርቱ ቃላት፡ በማንኛውም፡ የወንድ ኾነ የሴት ሰብአዊ ፍጡር፡ የልቡና [የነፍስ] ጽላት ላይ፡ በተፈጥሮ የተጻፉ ሲኾኑ፥ ነገር ግን፡ ጥንት፡ በኖኅ ዘመን፥ በመካከሉም፡ በሎጥ ዘመን፥ ዛሬም፡ በአኹኑ ትውልድ ዘመን ኾኖና እየኾነ፥ ደርሶና እየደረሰም በሚታየው ነውጥና ጥፋት፡ ከኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ልጆች በቀር፡ በምድር በሚኖሩ ሰዎች ኹሉ ዘንድ፡ ፈጽመው ተንቀው እንደተተዉ፡ በይፋ ይታወቃል።*

*ይህ ኹሉ ዝክረ ነገር፡ በተለይ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ታውቆና ታምኖበት የተኖረ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ እውነታ ስለኾነ፡ አንባቢዎቻችን፡ ከዚህ ጋር ነክነት ያላቸውን መልእክቶቻችንንና ማብራሪያዎቻችንን፡ እንዲመለሱባቸውና እንዲያጤኗቸው ከማሳሰብ በቀር፡ እዚህ ላይ፡ ከዚህ ያለፈ ሓተታን ማከሉ የሚያሻ አልመሰለንም።*

***እግዝእተብሔር እም*** *ለተዋሓደቻት፡ ለአምላካዊቷና ለኪዳናዊቷ፥ ለዘለዓለማዊቷና ለአማናዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ቀዳሚ አርአያና ምሳሌያዊት ጥላ የኾነችው፡ ይህች፡ ኦሪታዊቷና ጊዜአዊዋ ታቦተ ጽዮን፡ በዚህ ጣዖታዊ መልኳ ተዘጋጅታ መገኘቷ፡ "በምንም ሚዛን፡ መልካም ነው!" ባይባልም፥ ቸሩ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር አምላክ ግን፡ ለእነዚህ፡ ለዓመፀኞቹ የአይሁድ ፍጡሮቹ መዳን ሲል፡ ራሱን፡ ለመስቀል የግፍ ሞት ከመዳረግ የባሰውን፡ ጣዖት እስከመኾን ያደረሰውን፡ የመጨረሻውን ውርደት በመቀበሉ፡ የማይኾነውና የማያደርገው ምንም ነገር እንደሌለ፡ ፍቅሩንና ቸርነቱን፡ በሚበቃ አሳይቷል።*

*ይህን የመሰለው፡ ፍጹም ፍቅርና ቸርነት የታየበት፡ ይህ መለኮታዊ ሥራ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንንና ምግባራችንን፥ ሥርዓታችንንና ትውፊታችንን፡ በጽኑ መቅደሳዊ ማኅደርነት፡ ለማቆየት፥ በጠንካራ መለኮታዊ ድልድይነትም ለማሸጋገር፥ በቋሚ ሓውልትነት ለማዘከርና በቀና ጐዳናም ለመቀጠል ያስቻለ በመኾኑ፡ ሊወደስ እንደሚገባው አያጠያይቅም።*

ይህም እውነታ፡ ፍጥረተ ዓለሙን፡ ለመጨረሻው የደኅንነትና የትንሣኤ ሕይወት ያበቃ ዘንድ፡ በኋለኛው ዘመን እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነታቸውና ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነታቸው፡ በተዋሕዶ ባደሩባት፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና በተወዳጁ ልጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ ለተፈጸመው፡ ለመለኮታዊዋ እናት መሥዋዕትነትና ለመለኮታዊ ልጇ ቤዛነት፡ መልካም ውጤታማነት፡ በቂ ማረጋገጫ ኾኗል።

የዚች የታቦተ ጽዮን አምላካዊ ተልእኮ፡ በእነዚሁ፡ እምቢተኞችና ዐንገተ-ደንዳኖች አይሁድ ዘንድ፡ የበለጠ ክህደትንና ዓመፀኝነትን፥ ተቃዋሚነትንና ክፋትን እንጂ፡ በምንም መንገድ፡ ተቀባይነትንና ተከባሪነትን፥ ተፈጻሚነትንና ፍሬያማነትን፡ ሊአስገኝ ስላልቻለ፥ እነርሱና ምድራቸውም፡ በተለይ፡ እንደገና ጽዋው በሞላው፡ የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢኣታቸው ምክንያት፡ መደምሰሳቸው፣ የቀሩትም፡ በምርኮ፡ ወደባዕድ አገር መሰደዳቸው የማይቀር መኾኑ፡ በመለኮታዊው ፍትሕ ርትዕ በታወቀ ጊዜ፡ የነበረው ብቸኛ ማማረጫ፡ ይህችኑ፡ ታቦተ ጽዮን፡ ወደተቀደሰው መቆያዋ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትመለስ ማድረጉ ኾነ።

ይህም እግዚአብሔራዊ ትድግና፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ቅድመ አያቷ መልከ ጼዴቅ ወደቈረቈራትና ኹለተኛ አገርዋ ወደኾነችው፣ ታቦተ-ጽዮን ወደምትገኝባትም፣ የእስራኤላዊው ዳዊትና የኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ ልጅ የኾነው ሰሎሞን፡ በንጉሥነት ወደሚያስተዳድራት፡ ወደኢየሩሳሌም ባደረገችው የጕብኝት ጕዞ፡ በፍሬያማነት እንዲፈጸም ኾነ።

በዚሁ፡ በተቀደሰውና በገነነው ንግሥታዊ ጕዞ፡ የኪዳናዊው ዳዊትና የኪዳናዊቷ የቤትሳባ ዘር ኾኖ፡ በአጼዩት ማክዳ ማሕፀን፡ ከሰሎሞን፡ በድንግልና የተፀነሠው፡ በሕዝባዊው አጠራር፡ "ምኒልክ" የተባለው፡ እብነ-መለክ፡ ቀደም ብሎ፡ በእናቱ ማሕፀን እያለ፡ ወደትውልድ አገሩ ተመልሶ፡ በዚያ ሲወለድ፥ የኋላ ኋላ ደግሞ፡ ይኸው ምኒልክ፡ ለዓቅመ-አዳም ሲደርስ፡ በእርሱ አማካይነት፡ ይህችው ታቦተ ጽዮን፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሳ ገብታ፡ በምድሪቱ ኹለንተና መዐዝናት ተዘዋውራ ከባረከች በኋላ፡ የመጨረሻ መቆያዋ፡ አክሱም ኾኖ፡ በዚያ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በፍጹም ታማኝነትና ባለአደራነት ስትመለክ ኖረች።

እኒያ የካዱትና ያመፁባት አይሁድ ግን፡ በንስሓ እንዲመለሱ፡ በኢትዮጵያዊው ነቢይ፡ በኤርምያስ፣ በኢትዮጵያውያኑ ደቀ መዛሙርቱ፡ በአቤሜሌክና በባሮክም አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተላለፈላቸውን የምክርና የማስጠንቀቂያ መልእክት፡ ሰምተው ለመቀበልና ለመፈጸም፡ "እምቢ!" በማለታቸው፡ እነርሱና ምድራቸው፥ ቤተ መቅደሳቸው ጭምር፡ በባቢሎናዊው ናቡከደነፆር ሰይፍ እየታረዱ ሲያልቁ፥ በጦር ኃይሉም እሳት ተቃጥለው ሲጠፉ፥ የተረፉት ደግሞ፡ ለሰባ ዓመታት፡ የስደት መከራ ተጻረጉ።

ይህችው ታቦተ ጽዮን፡ በተቀደሰችው፡ የኢትዮጵያ ምድር፥ በቅዱሳኑና በቅዱሳቱ የኢትዮጵያ ልጆችዋም ዘንድ፡ ተከብራና ተወድዳ፥ በአግባቡ ስትመለክ ከኖረች በኋላ፡ የ፳ሺ፳፻ው ዘመነ ፍዳ አብቅቶ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል ኪዳኑን፡ ለፍጥረቱ ኹሉ የሚያቀዳጅበት፡ ዘመነ ሥጋዌ በተቃረበበት ጊዜ፡ በእግዚአብሔር አብና በእግዝእተብሔር እም፥ በእግዚአብሔር ወልድና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ መለኮታዊ ሥልጣንና ተአምራዊ ጸጋ፡ ራሷን ለፍጹሙ ንጽሓ ባሕርይ ባበቃችው በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት ላይ የተፈጸመውን፡ ሌላውን፡ ታላቁን፡ ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ ትንግርት ደግሞ፡ እስኪ እናብሥራችሁ!

ይኸውም፡ "ጽላተ ሙሴ፥ ጽላተ ኪዳን"፥ ወይም፡ "ታቦተ ጽዮን" በተባለችው፡ በዚችው፡ ኹለት ሰሌዳዎች ባሏት፡ የዕብነ በረድ ቅርጾች ላይ፡ ራሱ ቃል እግዚአብሔር፡ ዐሥሩ ቃላት ኆኖ ከመጻፉ በፊት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቀድማ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እነዚያን ኹለት የዕብነ በረድ ሰሌዳዎች እንደተዋሓደች ይታወሳል። በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ልክ በሥጋዌው ጊዜ፡ ድንግል ማርያም፡ እግዚአብሔር ወልድን ከመፅነሷ በፊት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቀድማ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ የዚችኑ፡ በንጽሕናና በቅድስና ፍጹም የበቃውን የድንግል ማርያምን ሰውነት እንደተዋሓደች ኹሉ፡ ማለት ነው።

አኹን፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ የ፳ሺ፳፻ው ዘመነ ፍዳ አብቅቶ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል ኪዳኑን፡ ለፍጥረቱ ኹሉ የሚያቀዳጅበት፡ ዘመነ ሥጋዌ በተቃረበበት ጊዜ፡ ያችው፡ ጽላቷን የተዋሓደችው፡ እግዝእተብሔር እም እና በእርሷ ላይ፡ ዐሥሩ ቃላት ኆኖ የተጻፈው፡ እግዚአብሔር ቃል፡ ኹለቱም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ጥበብ፡ ተነሥተው፡ ከጽላቷና ከታቦቷ ጋር፡ ራሷ፡ ሕያውት የድንግል ማርያም ፍጹም ሰውነት ኾኑ።

ፍጹም ንጽሕትና ቅድስት በኾነችው፥ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሳ በምትወልደው፡ በዚያች፡ የድንግል ማርያም ሰውነት፡ እግዝእተብሔር እም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልዩ ግብር፡ በቅድሚያ ተዋሐደቻት። ከዚያም፡ ምንም የሚሳነው በሌለ፡ በእግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ ሥራ፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ቅዱስ ሥርዓት ተወስነው፡ እዚያው፡ አኵስም ይኖሩ በነበሩት፡ በኢያቄም አብራክ እና በሓና ማሕፀን ዐርፋ፡ ሕፃን ማርያም፡ በታኅሣሥ ፯ ቀን፥ ፳ሺ፩፻፹፫ ዓመተ ኪዳን ተፀነሰች።

በምክነታቸው ምክንያት ሲያዝኑና ሲተክዙ፥ በሃይማኖት ተስፋና በምግባራዊ ሕይወት፡ ጸንተው፡ ዘወትር ሲጸልዩና አምላካቸው እግዚአብሔርን፥ "እምነ ጽዮን! እናታችን ጽዮን" የሚሏትን፡ ታቦተ ጽዮንንም ሲማፀኑ የኖሩት፡ ኢያቄምና ሓና፡ በታላቅ ደስታ ተመልተው፡ ወዲያው፡ በዐቃቤ መልአካቸው፡ በቅዱስ ገብርኤል እየተጠበቁና እየተመሩ፡ ጉዟቸውን፡ ወደኹለተኛዪቱ አገራቸው፡ ወደኢየሩሳሌም ሊያደርጉ፡ ከአኵስም ተነሡ። በረዥሙ መንገዳቸው፡ ዱር ለዱር ሲጓዙ ቆይተውም፡ ምድረ ከነዓን፡ በደኅና እንደደረሱ፡ ብዙም ሳይቆዩ፡ ሕፃን ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ባለ የተክል ቦታ፡ በመስከረም ፩ ቀን፥ ፳ሺ፩፻፹፬ ዓመተ ኪዳን፡ ተወለደች።

በዚህ ኹኔታ፡ ይኸው መልአክ፡ እንዲህ እየጠበቃቸውና እየመራቸው፥ ሕፃኒቱ ማርያም፡ የእናቷን ጡት እየጠባች፥ ወላጆቿም፡ የአንዲት ቅንጣት የምክነት ልጃቸውን ጽኑ ፍቅር፡ እርሷን በማቀፍና በመሳም እየተወጡ፡ ለሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ያህል፡ በእየጥሻው በሚሠሩት ዳስና በእየዋሻው በሚቀልሱት ጎጆ እየኖሩ ከቆዩ በኋላ፡ በታኅሣሥ ፫ ቀን፥ ፭ሺ፬፻፹፯ ዓመተ ኪዳን፥ ይኸውም፡ የዛሬ ፩ሺ፱፻፺፮ (አንድ ሺህ፡ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስድስት) ዓመታት፡ ሕፃን ማርያም [እመ-አርያም]፡ አማናዊቷና ሰብአዊቷ፥ ሕያውቷና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ ጽላተ ኪዳን ኾና፡ ወደኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደሷ ተመልሳ ገባች።

በዚያች፡ በጽላተ ኪዳኗ ላይ ተቀርጾ፡ በዚያች፡ በታቦተ ጽዮን (ሣጥን) ማደሪያው ውስጥ ተቀምጦ የኖረው፡ እግዚአብሔር ቃል፡ በታኅሣሥ ፮ ቀን፥ ፭ሺ፬፻፺፱ ዓመተ ኪዳን፡ በመልአኩ፡ በቅዱስ ገብርኤል ምሥራች፡ አማናዊው ሰው ኾኖ፡ የ፲፭ (ዐሥራ አምስት) ዓመት ቆንጆ በኾነችው፡ በኢትዮጵያዋ ድንግል እመአርያም ማሕፀን እስኪፀነስ ድረስ፥ ከዚያም፡ ይህችው ቅድስት ድንግል እመአርያም፡ ሮማዊው ቄሣር አውግስጦስ፡ ትንቢቱን ሊያስፈጽም፡ ባወጣው ዐዋጅ መሠረት፡ በጻድቁ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ዮሴፍ ጠባቂነትና በጻድቂቱ ኢትዮጵያዊት ሰሎሜ አገልጋይነት፡ ወደቤተ ልሔም ተጕዛ፡ የዓመተ ምሕረቱ መግቢያና የመጀመሪያው ዕለት በኾነው፡ በመስከረም ፮ ቀን፥ ኢትዮጵያዊ ሕፃን ልጇን ኢየሱስ መሲሕን፡ በበረት እስክትወልደው ድረስ፡ መኖሪያዋ በኾነው፡ በዚያ፡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ቆየች።

## "ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!"
## ስለሚለው ሃይማኖታዊ ይትበሃል፥

የኢትዮጵያ ልጆች፡ በግእዙ፡ "ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!"፥ በነጠላው ኢትዮጵያኛ ትርጕሙም፡ "ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" እያሉ፡ ዘወትር፡ በዜማ የሚያሰሙት ጸሎታቸው፡ ምንድር ነው?

እርሱማ፡ የዓለም መድኃኒትነቱን፡ ለእናቲቱ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፥ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ፡ ሰላም ማስገኘቱን ደግሞ፡ ለልጇ ለወዳጇ፡ ለወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ መሲሕ በመስጠት፡ በምስጋናና በውዳሴ፡ የሚጸልዩትና የሚዘምሩት፡ የምሥራች ቃል ሲኾን፡ ይኸው፡ የምሥራች ቃል፡ ከላይ ጀምሮ፡ እስካኹን ሲታተት፡ ከዚህ ከደረሰው፥ የኢትዮጵያ ልጆችም፡ አምነው ከተቀበሉት፡ ከእግዚአብሔርዋ እውነት የመነጨ ነው።

ዓለሙን የማዳኑ ቀዳሚ ድርሻ፡ የእናቲቱ መኾኑን፡ ቃሉ፡ "**መድኃኒት**" በሚለው በአንስታይ አንቀጽ በመነገሩ፡ ተጨማሪ ማስረጃነቱ፡ በዚህም ይታወቃል። የወንድ ሲኾን፡ ቃሉ የሚነገረው፡ "**መድኅን**" ተብሎ ነውና።

ይኸውም፡ እጅግ በጸናው ክፋቱና እጅግ በበዛው ኃጢአቱ ምክንያት፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ውጪ ኾኖ የጠፋው ፍጥረተ ዓለም **የዳነው፡** በእርሷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም መኾኑ የተረጋገጠው፡ **ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሱን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ከመጽነሷ በፊት፡ እግዝእተብሔር እም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አስቀድማ ልትዋሓዳት አስፈላጊ ኾኖ፡ ይኸው ተዋሕዶ፡ በዚህ መልክና ይዘት ሊፈጸም በመቻሉ ነው።**

ይህንም መለኮታዊ ትንግርት፡ በበለጠ ለማብራራት፡ **ድንግል ማርያም፡ በራሷ ፍላጎትና ምርጫ፥ በራሷ ቍርጥ ውሳኔና አድራጎት፡ ራሷን፡ በእግዚአብሔር መልክ ለተፈጠረችበትና በእግዚአብሔር ቃል፡ "ከእኛ እንዳንዱ ኾነች!" ለተባለችበት ፍጹምነት አብቅታ በተገኘችበት ጊዜ፡ በቅድሚያ፡ እግዝእተብሔር እም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እርሷን፡ ድንግል ማርያምን ተዋሓደቻት።**

ልክ፡ ይህች የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በተፈጸመባት አፍታ ነው፡ "**ብኪ ድኅነ ዓለም**፤ ዓለም፡ በአንቺ ዳነ!" የሚለው የምሥራች ዐዋጅ የታወጀውና የተፈጸመው። **አለዚያ፡ የሰብአዊ ፍጡር አካልና ባሕርይ፡ የእግዚአብሔርን፡ አካልና ባሕርይ ሊዋሓድና ሊያስገኝ፥ ሊወልድና ሊያሠርፅ አይቻለውም።** ስለዚህ፡-

፩ኛ፡ **የእግዚአብሔር የማዳኑ ምልክትና የምሕረቱ ማረጋገጫ፡** ይህ የእግዝእተብሔር እም፡ መለኮታዊ አካልና ባሕርይ፡ በምሥዋ'ዐ-መድኃኒትነት፡ ከድንግል ማርያም የሰውነት አካልና ባሕርይ ጋር በተዋሕዶ አንድ መኾኑና መክበሩ ኾኖ ተገኘ።

፪ኛ ደግሞ፡ **እውነተኛውና ፍጹሙ፥ ዘለዓለማዊውና እግዚአብሔራዊው ሰላም የተገኘው፡** በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሲሕ ብቻ መኾኑ የተረጋገጠው፡ እርሱ፡ ራሱ ኢየሱስ መሲሕ፡ ኃጢአትንና ሞትን ላስከተሉት፡ ለክፋትና ለሓሰት፡ ምንጭና አባት ከኾነው፡ ከዲያብሎስ ጋር፡ ከአዳም እና ሔዋን ፍጥረት በፊት አንሥቶ፡ መጀመሪያ፡ በመንፈስ እና በነፍስ፤ ኋላም፡ በሥጋ፡ ሲያካኺድ የኖረው ጦርነት፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም፡ አንድያ ልጅ የኾነው፡ እርሱ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ላይ፡ የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ ታርዶ፤ ሥጋውን በመቍረስ፥ ደሙንም በማፍሰስ፡ በፈጸመው ቤዛነቱ፡ የሰላም ባለቤትነቱ ድል አድራጊነት፡ እንዲህ ስለተጠናቀቀ ነው።

ስለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ማንነት፡ እስከዚህ በተሰጠው ሓተታ፡ የተገለጸውን እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ቃል ያጠቃልለዋል፡-

**"ወይቤላ መልአክ፡- 'ኢትፍርሂ ማርያም! እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር። ወናሁ ትፀንሲ፤ ወትወልዲ ወልደ፤ ወትሰይሚዮ ስሞ፡ "ኢየሱስ"፤ ውእቱ ዐቢይ፤ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል፤ ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ፡ መንበረ ዳዊት አቡሁ፤ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።'"**

**"ወትቤሎ ማርያም፡ ለመልአክ፡- 'እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ፡ እንዘ ኢየአምር ብእሴ!?**

**"ወአውሥአ መልአክ፡ ወይቤላ፡- 'መንፈሰ እግዚአብሔር ቅዱስ፡ ይመጽእ ላዕሌኪ። ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ። ወዘኒ፡ ይትወለድ እምኔኪ፡ ቅዱስ ውእቱ። ወይሰመይ፡ ‹ወልደ እግዚአብሔር ልዑል›። ወናሁ ኤልሣቤጥኒ፡ እንተ እምአዝማድኪ፡ ይእቲኒ ፀንሰት፤ ወረከበት ወልደ፡ በልህቃቲሃ፥ ወበርስአቲሃ።**
**ወናሁ ሳድስ፡ ዝንቱ ወርኀ፡ ለእንተ ይብልዋ መካን። እስመ አልቦ ነገር፡ ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር።'**

**"ወትቤሎ ማርያም፡ ለመልአክ፡- 'ነየ፡ ዓመተ እግዚአብሔር! ይኩነኒ፡ በከመ ትቤለኒ!'**

"መልአኩም፡ 'ማርያም ሆይ! አትፍሪ! በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ሞገስን አግኝተሻልና። እነሆ! ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም፡ 'ኢየሱስ' ትዪዋለሽ። እርሱም፡ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ስለኾነ፡ ታላቅ ነው። እግዚአብሔር አምላክም፡ የአባቱን፡ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ፡ ለዘለዓለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም፡ ፍጻሜ የለውም።' አላት።

"ማርያምም፡ መልአኩን፡- 'ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ፡ እንዴት ይኾንልኛል!?' አለችው።

"መልአኩም መልሶ፡ እንዲህ አላት፡- 'የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ፡ በአንቺ ላይ ይመጣል። ቅዱስ እግዚአብሔር አብም፡ በልዑል ኃይሉ ያቅፍሻል። ስለዚህ፡ ከአንቺ የሚወለደው እርሱ፡ አንዱ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ነው፤ ‹የልዑል እግዚአብሔር አብ ልጅ›ም ይባላል። እነሆ! ከዘመዶችሽ አንዷ፡ ‹ኤልሣቤጥ›፡ እርሷም እኮ! በዚህ፡ ባፈጀ ዕድሜዋና እርጅናዋ፡ ፀንሳ፣ ወንድ ልጅን አግኝታለች። እነሆም! ‹መኻን!› ለሚሏት፡ ለእርሷ፡ ይህ ፅንሷ፡ ስድስት ወር ኾኖታል። ለእግዚአብሔር፡ የሚሳነው ነገር የለምና።'"

"ማርያምም፡ መልአኩን፡- 'እነሆኝ እኔ! የእግዚአብሔር ባሪያ! እንዳልኸኝ፡ ይኹንልኝ!' አለችው።"

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፥ እንደወንዱም፥ እንደሴቱም፡ ፈጣሪ አምላክ፡ **"በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነም!"** በተባለለት በዚያ ሰውነቷ፡ ከኢያቄም አብራክና ከሓና ማሕፀን ጀምራ፡ እግዚአብሔርን መስላ ለተገኘችበት ፍጹምነት፡ ራሷን፡ አብቅታ በመገኘቷ፡ ይኸው፡ በቅድሚያ፡ የእግዝእተብሔር እም መለኮታዊ ውሕደትን የተጐናጸፈች ኾነች፤ ከዚህ የተነሣም፡ **"አምላክ፡ ሰው ኾነ! ሰውም፡ አምላክ ኾነ!" ለሚለው፡ ለተዋሕዶው ሃይማኖታዊ ዘይቤ፡ የመጀመሪያዋ፡ ሕያውት መሠረት፣ ምዕራፍና መጽሔት ኾነች።**

ከላይ የተጠቀሰውን፡ የልዑል እግዚአብሔር፡ ባለሟል የኾነውን፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን፡ የምሥራች ቃል ለመስማትና ለመቀበል፥ ለመፈጸምና ለፍሬ ለማብቃትም፡ በጠቅላላ፡ ከሰዎች፥ በተለይም፡ ከሴቶች መካከል፡ የመጀመሪያዋ ድንግል ኾነች።

ይህን፡ የመልአኩን፡ የምሥራች ቃል ተከትሎ፡ የኾነው ኹሉ፡ ይህችው ኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ **'ወንድ ስለማላውቅ፡ ይህ፡ እንዴት ይኾንልኛል!?'** ብላ ላቀረበችለት ጥያቄ፡ መልአኩ፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ለመውለድ፡ በእግዚአብሔር አብና በእርሷ መካከል ስለሚኾነው ምሥጢራዊ ጉዳይ፡ በማስረጃ ያመላከታት፡ እንዲህ በሚል ቃል፡ ሊገለጽ በተቻለው ኹኔታ ነበር።

ይኸውም፡ በመለኮታዊው ሥርዓተ ጋብቻ ተወስነው፡ ነገር ግን፡ ያለፍሬ፡ ለረዥም ዘመን፡ በባልና ሚስትነት የኖሩት፡ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ፡ በዚያ፡ ባፈጀው፡ የእርጅና ዕድሜያቸው፡ ልጃቸውን፡ መጥምቁ ዮሓንስን ለመውለድ፡ "ምንም የማይሳነው" የተባለው እግዚአብሔር፡ በኹለቱ፡ ማለትም፡ በዘካርያስና በኤልሣቤጥ ሰውነት ባሳደረው የፍትወት ስሜት ተገፋፍተው፡ በመካከላቸው፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን እንዲያደርጉ ባስቻላቸው ዓይነት፡ ይህም፡ መንፈስ በኾነው መለኮት እና በፍጹም፡ የኹለንተና ብቅዓቷ፡ እግዝእተብሔር እም በተዋሓደችው፣ ከዚህ የተነሣም፡ ወደመንፈሳዊው የመለኮት ህልውና የመለወጥ ኃይልን በተቀዳጀው ትስብእት መካከል፡ በቀደመው መለኮታዊ የጋብቻ ሥርዓት ጊዜ እንደኾነው ኩነት፡ አኹንም፡ እንደዚያው የሚፈጸም ስለመኾኑ፡ የሰጣት መግለጫ ነበር።

መልአኩ፡ ያን ኹኔታ ማስረጃ አድርጎ ስላቀረበላት፡ እርሷም፡ ያን ማስረጃ፡ ለጥያቄዋ በቂ መልስ እንደኾነ አድርጋ በእምነት ስለተቀበለች፡ እንደመልአኩ የምሥራች ቃል፡ ጥንት፡ በመጀመሪያ፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ በእግዝእተብሔር እም-ነቷ፡ ‹እግዚአብሔር ወልድ› በተባለበት ማንነቱ፥ በመካከለኛው የፍጥረት ዘመንም፡ በእርሷ የታቦተ ጽዮኗ ጽላትነቷ ላይ፡ በእግዚአብሔር ቃልነቱ፡ ተጽፎ ሲመለክና በአምላክነቱ ሲሠራ የኖረው፡ ያው አንዱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ አኹን፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ "ኢየሱስ መሲሕ" ተብሎ፡ ከዚችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት በወለደችው ጊዜ፡ መለኮታዊውና ትስብእታዊው አባቱ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር አብ፥ መለኮታዊዋና ትስብእታዊዋ እናቱ ደግሞ፡ እርሷ፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗ፡ እውንና እሙን ኾኖ ተረጋገጠ።

"ወልደ አብ ፡ ወልደ ማርያም፡ የአብ ልጅ ፡ የማርያም ልጅ" የኾነውና የተባለው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመለኮትና የትስብእት ወላጆቹ ከኾኑት፡ ከእግዚአብሔር አብ አባቱ እና ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እናቱ፡ እንዲህ ተወልዶ፥ እርሷ፡ ቅድስት እናቱም፡ በመስቀሉ ሥር ሳይቀር በመቆም፡ ለአንዲት ቀን እንኳ ሳትለየው፡ በመጨረሻ፡ ተቃዋሚዎቹን ኹሉ፡ በድል አድራጊነት አሸነፈ።

በቤዛነቱ የፍቅር ኃይል፡ ዲያብሎስን፥ የእርሱ የክፋት ሠራዊቱ የኾኑትን፡ ርኵሳን መናፍስቱንና ሰብአውያን ግብረ-ዐበሮቹን ጭምር፡ ለ፶፫ ዓመታት ያህል እየታገለ በመዋጋት፡ ከምድረ ገጽ አስወገደ። **ከመጀመሪያውም፡ በፈጣሪ ተመሥርታ የኖረችው፡** <u>**ፍጹሟ እና ዘለዓለማዊቷ ሰላም፡**</u> በዚሁ ህልውናዋ ጸንታ እንዲህ፡ እንድትቀጥል አደረገ።

ነፍሳዊዉንና ሥጋዊዉን፥ መንፈሳዊዉንም የድል አድራጊነት መሣሪያ፡ ለቅዱሳንና ለቅዱሳት የኢትዮጵያ ልጆች ሐዋርያቱ፥ ላመኑበት ተከታዮቹም ኹሉ ካስረከባቸው በኋላ፡ ራሱም፡ መንፈስ ቅዱስ ኾኖ እስኪመለስ ድረስ፡ እርሷ፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመካከላቸው ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው ባሉበት፡ በዓይናቸው እያዩት፡ ወደሰማይ ዐረገ።

ባረገ፡ በዐሥረኛውም ቀን፡ አኹንም፡ እርሷ፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በእኒሁ ሐዋርያቱና ባመኑበት ተከታዮቹ መካከል ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው ሣሉ፡ "**አንትሙሰ ትጠመቁ፡ በመንፈስ ቅዱስ!** እናንተ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ!" ብሎ የሰጣቸውን፡ የተስፋ ቃሉን በመፈጸም፡ በኹሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ኾኖ ወረደባቸው፤ ተዋሐዳቸውም። (የሐዋ. ፩፥ ፬-፰። ፪፥ ፩-፬።)

ከዚህ በኋላ፡ እርሷ፡ ዋና ማእከላቸውና ሰብሳቢያቸው በመኾኗ፡ የእርሷና የእርሱ የኾነችውን፡ **የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታቸውን ምሥራች፡** ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ ለማዳረስ፡ እኒሁ ሐዋርያቱና ያመኑበት ተከታዮቹ፡ በእየአህጉሩ ተበታተኑ። ተልእኳቸውን እየፈጸሙ ሲመለሱም፡ በእርሷ ዙሪያ እየተሰበሰቡ፡ ተልእኳቸውን ሲያስፋፉ፡ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ዐብረዋት ኖሩ።

መቸም፡ አይሁድ፡ ኢትዮጵያዊው መሲሕ ኢየሱስ፡ በሥጋውና በደሙ የዋጃትና ዐትሞ ያጸናት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** እየተስፋፋች የመኼዱን ኹኔታ በሚያዩበት ጊዜ፡ ዝም ብለው እየተመለከቱ መቀጠልን፡ ሊቋቋሙት የሚቻላቸው ኹኔታ ሳይኾንላቸው ቀረ። ይህ አሥጊ ኹኔታ፡ የክፉ ቅንዓት፡ ነበልባላዊ እሳትን፡ በውስጣቸው ስለኮሰተረባቸው፡ የመጥፋታቸው አደጋ ኾና የተጋረጠችባቸውና በእነርሱ ዘንድ፡ ለሰላማቸው፡ ጠንቅ ኾና ያገኟት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አረጋገጡ። በዚህ ጊዜ፡ እርሷን ለማስወገድ የሚያስችላቸውን ዘዴ ሲፈልጉ፡ ቀደም ብለው፡ በተወዳጁ ልጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ ላይ የተጠቀሙበትና የፈጸሙበት ግፍ፡ በቅርብ ተከሠተላቸው። ስለዚህ፡ አኹንም፡ ያንኑ ዘዴ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱም ላይ ለመፈጸም ይዘጋጁ ጀመር።

ይህን ክፉ ዕቅዳቸውን ያወቀ መንፈስ ቅዱስ፡ ይህንኑ ውጥናቸውን፡ በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት፡ "እመ-እግዚአብሔር ጸባዖት" [እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትና የአሸናፊው፡ የእግዚአብሔር እናት ለመኾን የበቃችው] ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በ፷፬ (ስድሳ አራት) ዓመቷ፡ በዚያው፡ በሕያውነቷ፡ ወደገነት የምትፈልስበት ጊዜ ስለደረሰ፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ ፵፰ ዓመተ ምሕረት፡ በሕይወተ ሥጋዋ እንዳለች፡ ወደገነት ተነጠቀች።

ይህ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለች፡ ወደገነት የመነጠቋ መለኮታዊ ትንግርት፥ ማለትም፡ የፍልሰቷ ዝክረ ነገር፡ በሚቀጥለው፡ ንኡስ አርእስት ሥር፡ ተገልጾ ታገኙታላችሁና አከታትላችሁ ተመልከቱት።

## "አስተርእዮ" ምን ማለት ነው? መልእክቱስ፡ ምንድር ነው"

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ መታሰቢያ በዓል፡ በየዓመቱ የሚውለው፡ ጥር ፳፩ ቀን ነው። እርሱም፡ "አስተርእዮ ማርያም" በሚል ስያሜ ይጠራል። በዓሉ፡ እንዲህ ባለ ስያሜ ሊጠራ ያስፈለገበትን ምክንያት ለማብራራት፡ ይኸው ምክንያት፡ **ታላላቅ የኾኑ** አምላካውያት ምሥጢራት የተከሠቱበትን ኹኔታዎች ያካተተ በመኾኑ፡ ሰፊና ጥልቅ ቢኾንም፡ በጥቂቱ ሳንገልጸው አናልፍም።

በመጀመሪያ ነገር፡ "አስተርአየ" የሚለው፡ የግእዙ ቃል፡ "አሳየ፤ ገለጠ፤ አበራ፤ ነገረ፤ አስተማረ፤ አሳወቀ፤ አስረዳ" ማለት ነው። "አስተርእዮ" የሚለውም ቃል፡ ከዚሁ የተገኘ ሲኾን፡ "የገለጠበት፥ የተገለጠበት፤ ያሳየበት፥ የታየበት፤" ማለት ነው። ምኑን የገለጠበትና ያሳየበት? ማንነቱን ነዋ! ምን ኾኖ፥ እንዴትስ ኾኖ የተገለጠበትና የታየበት? ይህ ኾኖ፥ እንዲህም ኾኖ የተገለጠውና የታየው፡ እርሱ፡ ማነው? "እውነትና መንፈስ የኾነው፡ እርሱ፡ የማይታየው፡ ፈጣሪና የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፡ በገሃድ ሊገለጥና በግዘፍ ሊታይ፡ ሰው ኾነ! በሰውነት ተገልጦ ታየ!" ለማለት፡ ይህ ኹሉ መለኮታዊ ትንግርት የተፈጸመበት ወራት፡ "አስተርእዮ" ተባለ።

ይህ አስተርእዮት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት የመገለጡና የመታየቱ ምሥጢራዊ ትንግርት የተፈጸመበትን ኹኔታ፡ እስኪ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል እናቅርበው!

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተፈጠረችበት፡ በእግዚአብሔር መልኳ፥ በእርሱ በፈጣሪዋም፡ **"ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነች!"** በተባለችበት አምላካዊ ማንነቷ፡ ራሷን፡ ለዚያ ፍጹምነት አብቅታ ተገኘች። እንዲህ፡ ፍጹም በቅታ ስለተገኘች፡ በመጀመሪያ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እግዝእተብሔር እም ተዋሓደቻት፤ ከዚያ በኋላም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡- ለሌላ ለማንም ፍጡር ተገልጦና ታይቶ ሊታወቅ ባልቻለ የአስተርእዮቱ ምስጢር፡ ከፈጣሪ በኩል፡ በቅድሚያ፡ ራሱ፥ ቀጥሎ፡ ከቅዱሳን መላእክቱ ወገን፥ ቅዱስ ገብርኤል፥ በመጨረሻ፡ ከሰዎች ፍጡሮቹ በኩል፡ ራሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እኒህ ሦስቱ ብቻ ባወቁት ክሥተትና ርእዮት፡ በትስብእትነት [በሰውነት] ተፀነሰ፤

ይኸም፡ እግዝእተብሔር እም በተዋሓደቻት፡ በእርሷው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ የኾነው፡ የፅንሰቱ ምሥራች በታኅሣሥ ፩ ቀን፡ ፭ሺ፬፻፺፱ ዓመተ ኪዳን ተነገረ።

ከዚያ ተያይዞ፡ የአስተርእዮቱን አድማስ በበለጠ በማስፋት፡ በፈጣሪ በኵል፡ ራሳቸው ቅድስት ሥላሴና በመንበረ ጸባዖቱ ዙርያ ያሉትን፥ በሱራፌልና በኪሩቤልም የታቀፉትን አርባዕቱ እንስሳን፥ ከቅዱሳን አንጋደ መላእክትም፡ ከነመንጎቻቸው፡ በሜዳ ሠፍረው በነበሩ እረኞች ዘንድ የታዩት፡ የሰማይ መላእክት፣ የምድር ሠራዊት ከኾኑት፡ ከሰው ወገኖች ደግሞ፡ ቅዱስ ዮሴፍና ቅድስት ሰሎሜ፥ እንዲሁም፡ ሕፃኑን ኢየሱስን ያሟሟቁት እንስሳት፥ እረኞቹም፡ ከነመንጎቻቸው፥ ከዚያም፡ እነሰብአ ሰገል ብቻ ባወቁት፡ የምሕረቱ ዓመት በባተበት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በሰውነት ተወለደ፤

እንዲህ፡ በፍጹም ሰውነት፡ እስካኹን፡ ለጥቂቶችና ለብዙዎች ብቻ የተገለጠውና የታየው እግዚአብሔር፡ አኹን ደግሞ፡ ይኸው፡ እውነተኛ ማንነቱና ምንነቱ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ በሙሉ፥ ለኹሉም፡ በይፋ ይታወቅ ዘንድ፡ በጥር ፩ ቀን፥ ፴ ዓመተ ምሕረት፡ ሰማዩ ተከፍቶና አባቱ እግዚአብሔር አብ፡ "**ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘአፈቅር፡ ዘቦቱ ሠመርኩ!** ቀድሞ፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በሰውነት፡ ከእግዝእተብሔር እም ቅድስት ድንግል ማርያም የወለድሁት፡ የምወድደው፥ በእርሱም ደስ የምሰኝበት ልጄ፡ ይህ ነው!" ብሎ ቃሉን በማሰማት፣

እናቱ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በወንዙ አጠገብ ቆማ፡ የራሷንና የእርሱን ማንነት፡ በእናትነቷ በማረጋገጥ፣

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ "**ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ፤ ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር፡ እንዘ ይወርድ፡ በአምሳለ ርግብ፤ ወነበረ ላዕሌሁ።** እነሆ! ሰማይ ተከፈተለት፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ፡ በርግብ አምሳል፡ ሲወርድ፥ በእርሱም ላይ ሲያርፍበት አየ።" እንደተባለለት፡ ከሰማይ ወጥቶ በሚበርር ርግብ ተመስሎ፡ ወርዶ፡ በላዩ ላይ በማረፍ፡

ራሱ አጥማቂው ዮሐንስም፡ "**ወበውእቱ፡ ያጠምቀክሙ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት!**" ማለትም፡ "በመንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም የሚያጠምቃችሁ፡ እርሱ ነው!!" ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ በማመልከት፡ ኹሉም፡ ስለማንነቱ መስክረውለት፥ በመጥምቁ ዮሓንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። (ማቴ. ፫፥ ፲፩-፲፯።)

በዚህ መልክና ይዘት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን በኾነው ፅንሰቱ የተጀመረውና በመስከረም ፩ ቀን በኾነው ልደቱ የቀጠለው፥ ሲካኼድ ቆይቶም፡ በጥር ፩ ቀን በኾነው ጥምቀቱ ያበቃው፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት በመገለጥና በመታየት የፈጸመው የቸርነት ሥራው፡ እየታሰበ የሚከበርበት፡ በተለይ፡ ከጥር ፩ እስከ "በዓለ-ኢትዮጵያ" (የቀድሞው ጾመ-ኢትዮጵያ=ጾመ-ነነዌ) መግቢያ ድረስ ያለው ወራት፡ "አስተርእዮ" ተባለ።

## የድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ ዜና።

## "ፍልሰታ" ምንድር ነው?

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት፥ ኋላም፡ በኢየሱስ መሲሕ ተገልጾ፡ ብዛታቸው፡ ሊቆጠር የማይቻል፡ መልካካም ነገሮችን፡ ላበረከተልን ፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር፡ እንደምናደርገው ኹሉ፥ "እግዝእተብሔራችን እና መድኃኒታችን፤ እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን" ስለኾነችው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በየጎሊናችን የምናስበው፥ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሐዋሳታችን የምንፈጽመውም ኹሉ፡ በየሕይወታችን ውስጥ፡ ዐብሮን ሕያው ኾኖ፡ ለዘወትር፡ ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ፡ በአንድ ቀን፥ ወይም፡ በአንድ ሳምንት፥ ወይም፡ በአንድ ወር፥ ወይም፡ በአንድ ዓመት ብቻ፡ የተወሰነ አይደለም።

አኹንም፡ እዚህ ላይ አቅርበን የምንጽፍላችሁ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን ዜና መዋዕሏን፡ በተለይ፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሓፍ ውስጥ፡ ተመዝግቦ የሚነበበውን፥ ልጇ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ እስካረገበትና መንፈስ ቅዱስ፡ በሓዋርያት ላይ፡ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውን ሳይኾን፡ ከዚያ በኋላ፡ በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው፡ ምድራዊ ሕይወቷ፡ በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ ካበቃበት፡ ከ"**ፍልሰቷ**"፡ ማለትም፡ ሕያው በኾነው በአካለ ሥጋዋ፡ ከምድር፡ ወደገነት ተነጥቃ ከተወሰደችበት ቀን ተነሥተን፡ የመጨረሻ የኾነውን፡ ዜናዋን ብቻ ይኾናል፤ እርሱም፡ ይህንኑ፡ የፍልሰቷን ዝክረ ነገር በምናስታውስባቸው፡ በእነዚህ የሱባዔያችን ኹለት ሳምንታትና የፍልሰትዋን በዓል በምናከብርባት፡ በዚያች ዕለት፡ እንዲህ በሚለው ቃል ይገለጻል፡-

የእናታችን፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት የኾነው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ በዕለተ እሑድ ነው። "ፍልሰት"፥ ወይም፡ "ፍልሰታ" የሚባሉት አርእስት ቃላት፡ "ፈለሰ" ('ለ' ሳይጠብቅ) ከሚለው፡ "ከቦታ ወደቦታ መዘዋወርን"፡ ማለትም፡ "አንድ ሰው፡ ካለበት ቦታ ተነሥቶ፥ ወይም፡ መኖሪያውን ነቅሎ፡ ወደሌላ ኼደ፤ ወይም፡ ተወሰደ!" የሚል ትርጕምን ከሚያመለክተው፡ ከግእዝ ዘር የተገኘ ዘይቤ ነው፤ በኢትዮጵያኛ፡ "ለ" ጠብቆ፡ "ፈለሰ" ያሰኛል። ከዚህ የተነሣ፡ **የቅድስት ድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ከምድር፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የመወሰዱን ተአምር ለማስረዳት፡"ፍልሰታ"** እንላለን።

ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተፈጽሞበት፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሶ የወለደውንና ዐጥብቶ ያሳደገውን፡ ያን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ አይሁድ፡ እጅግ በከፋው አላዋቂነታቸውና ሰይጣናዊ አስተሳሰባቸው፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ ነው።

ለእነርሱ መዳን ሲል፡ በሰውነት መጥቶ፡ ያን፡ የሰላመ-መስቀል ቤዛነት ተልእኮውን ፈጽሞ፡ ወደክብሩ በተመለሰው፡ በልጇ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ ሰውነት ላይ፡ አድርገውት የነበረውን፡ ያንኑ ግፍና ጭካኔያቸውን፡ አኹንም፡ በዚያ፡ በእርሷ መለኮታዊ ሰውነት ላይ ለመፈጸም ባሰቡበት፥ በማሰብም ብቻ ሳይወሰኑ፡ አዎን! በሞከሩበት ጊዜ እንጂ።

እርሷንስ፡ እንኳን ሞት፡ አንዳችም ጉዳት፡ የጨረፍታ ያህል እንኳ፡ ሊያልፍባት እንደማይቻል፡ አይሁድ፡ አኹንም፡ አላወቁም። ገና ከመጀመሪያው፡ በፍጹም ሃይማኖቷና ምግባሯ፡ ሰውነቷን ለአምላክነት በማብቃቷ፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትን፥ የእግዚአብሔር አብ ሙኸሪት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አንድዮ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በመለኮትነት፥ ከፍጥረተ-ዓለም በኋላም፡ በሰውነት የወለደችለትን፡ የእርሷን፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ሰውነት፡ እንዴት፡ ክፋትና ኃጢአት፥ ሞትና መቃብር፥ መበስበስና ሌላውም ዓይነት ጉዳት፡ እንኳንስ ሊደርስበት፡ ሊቀርበውም እንኳ፡ አዎን! እንዴት ይቻለዋል? ፈጽሞ አይቻለውም።

እንኳንስ እርሷ፡ በእርሷና በልጇ በማመን፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁት ኹሉ እንኳ፡ በእርሷና በልጇ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ምክንያት፡ ከክፋትና ከኃጢአት፥ ከሞትና ከመቃብር መበስበስ ሳይቀር፡ ነጻ ኾነው፡ ምንም ዓይነት ጉዳት በሌለበት፡ በዘለዓለሚቱ የሰንበት ዓለም፡ ቅድስቲቱን የትንሣኤ ሕይወት፡ እንደሚኖሩ፡ አዎን! ገና አላወቁም።

እርሷም፡ እነዚያ አይሁድ፡ በእርሷ ሰውነት ላይ ሊያደርጉ ያሰቡትን፥ አስበውም አልቀረ፡ የቃጡትን፡ ያን ጉዳት ሊያደርሱ እንደማይቻላቸው፡ በመለኮታዊው ኃይሏ፡ እንደሚሰማቸው አድርጋ፡ አሳወቀቻቸው።

ከዚህ በኋላ፡ በመላእክት ተነጥቃ፡ ወደገነት ተወሰደች።

ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ አዎን! ይህ መለኮታዊ ትንግርት ከተፈጸመበት፡ ከፍልሰቷ ዕለት፡ ከጥር ፳፩ ቀን፣ ፴፰ ዓመተ-ምሕረት አንሥቶ ነው።

"መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ"፥ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የምንላት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንዲህ፡ በመላእክት ተነጥቃና በሰማያዊ ይባቤ ታጅባ፡ ወደገነት በፈለሰች፥ [በተወሰደች] ጊዜ፡ የኾነውን ደግሞ እንስማ!

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፡ ቅዱስ ሥጋውን እየቆራረሰና ክቡር ደሙንም እያፈሰሰ፡ የሰላም ቤዛነቱን ተልእኮ እየፈጸመ ባለበት ሰዓት፡ ከመስቀሉና ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አጠገብ ሳይለይ፡ የዚሁ ልጇን አደራነት ተቀብሎ፡ እርሷን፡ እናት፥ ራሱንም፡ ልጇ አድርጎ፡ ይጠብቃት የነበረው፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ አኹንም፡ ዐብሯት ኾኖ፡ ይህንኑ የፍልሰቷን ምስጢር ለማየት የበቃ ኾነ።

ሌሎቹ ሐዋርያት ግን፡ ይህን ታላቅ ተአምር ባለማየታቸው፡ በሚቀጥለው፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ የኹለት ሳምንት ሱባዔን ጀመሩ።

ይኼም ሱባዔያቸው፡ የነገሩን ኹሉ፡ እውነተኛ ምስጢር ስለገለጠላቸው፡ ፍሬያማውን ምላሽ ማግኘት እንደቻሉ አረጋገጡ። እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በነሐሴ ፲፬ ቀን፡ በዕለተ እሑድ፡ በዚያው፡ በሕያዉ ሰብአዊ አካሏ እንደገና፡ ወደምድር መጥታላቸዋለችና።

በልጇ ትንሣኤ ጊዜ እንደኾነውም፡ በመካከላቸውም ተገኝታ፡ "ሰላም ለኵልክሙ!"፡ ማለትም፡ "ሰላም፡ ለእናንተ ይኹን!" አለቻቸው። ያም ኹኔታ፡ ለሐዋርያት፡ ያን፡ የአምላካቸውንና የፈጣሪያቸውን፥ የመምህራቸውንና የሰላማቸውን፡ የኢየሱስ መሲሕን ትንሣኤ አስታወሳቸው። የእርሷንም፡ በዚህ፡ እውን በኾነው ሕያው ማንነቷ፡ ድንገት ተገልጣ፡ በመካከላቸው የመገኘቷን ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ እንደትንሣኤዋ አድርገው፡ በታላቅ ሐሤት ተቀበሉት።

እርሷም፡ ከዚያ አያይዛ፡ በብዙ የምሥራች ቃላት፡ እኒህኑ ሐዋርያትን፡ አጽናናቻቸው። እነርሱም፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ ከእርሷ ጋር፡ እስከነሐሴ ፲፮ ቀን ድረስ፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፡ ዐብራቸው ቆየች። በዚያኑም ዕለት ተሠወረቻቸው።

ከዚህ በኋላ፡ አልፎ አልፎ፡ በየግላቸውም ኾነ፡ በጋራ እየተገለጠችላቸው፡ እርሷ ስላወቀቻቸውና ስላየቻቸው፡ ስለብዙዎች መለኮታውያት ምሥጢራት፥ ደግሞም፡ አኹን እርሷ፡ ለእነርሱ የተገለጠችበት ኹናቴ፡ እንደልጇ ትንሣኤ ኾኖ መቅረቡን አምነው እንዲቀበሉት፡ ለዓርባ ቀናት ያህል፡ ስታሳውቃቸውና ስታነቃቃቸው ሰነባበተች።፡

ይህን ሕያው ፍልሰታዋን፡ እንደልጇ ትንሣኤ አድርጋ እንደገለጠች ኹሉ፡ ዕርገቷንም እንዲሁ፡ እንደልጇ ታደርግ ዘንድ ፈቃዱ ስለኾነ፡ የሕያው ትንሣኤዋን እውነታ፡ ማሳወቅ የጀመረችበትን፡ ነሐሴ ፲፬ ቀንንና የጨረሰችበትን፡ ነሐሴ ፲፮ ቀንን፡ እነዚህን፡ ሦስት መዓልታትና ሦስት ሌሊታት መነሻ በማድረግ፡ በአርባኛው ዕለት፡ በመስከረም ፳፭ ቀን፡ እንደልጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደሰማይ ዐረገች።

በጥር ፳፩ ቀን ተጀምሮ፡ በመስከረም ፳፭ ቀን ያበቃውን፡ የፍልሰቷን ነገር አካትቶ ለማዘከር ተብሎ፡ የተመደበ ቃል ነው፡ ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ዘይቤ።

የመለኮት ድንቅ ምሥጢራዊ ኃይል የኾነው፥ በልጇ፡ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ ብኵርናና ቀዳሚነትም የተጀመረው፡ ይህ፡ የትንሣኤና የዕርገት ነገር፡ አኹን ደግሞ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱ ድንግል ማርያም፡ ገሃድና እውን ኾኖ የታየበትን፡ ይህን ዕርገቷን ለማየትና ምስክር ለመኾን የታደለው፡ ቀድሞ፡ የልጇን ትንሣኤ የመጀመሪያ ምሥራች፡ ከቀሩት ሐዋርያት ጋር ለመስማትና ለማየት፡ ሳይታደል ቀርቶ የነበረው፡ ሐዋርያው ቶማስ ብቻ እንደነበረ ይታወሳል።

አኹን ግን፡ የፍልሰት ትንሣኤዋን ባያይም፡ ዕርገቷን ለማየት፡ ከቀሩት ሐዋርያት መካከል፡ ተለይቶ የታደለው፡ ይኸው፡ ሐዋርያው ቶማስ ብቻ ኾኖ ተገኘ።

ከቶማስ ጋር የተያያዘው፡ የዚህ ርእስ ዝክረ ነገር፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ማለትም፡ በመጀመሪያው ሱባዔ ጊዜ፡ ሐዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም። ለሐዋርያት በተሰጣቸው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል፡ እርሱም እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት፡ ዘግይቶ፡ በዚያ በደመናው እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሐዋርያት ሲመጣ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እያረገች ሣለች፡ እርሷ ባሰበችው በጎ ምክንያት፡ ለእርሱ፡ ለቶማስ ተገለጠችለት።

"ያችም ዕለት፡ ለሐዋርያት፡ እንደልጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ የእርሷም፡ የፍልሰት ትንሣኤዋ የኾኑላቸውን፡ ከነሐሴ ፲፬ እስከ፲፮ ቀን ያሉትን፡ ሦስት መዓልታትና ሦስት ሌሊታት መነሻ በማድረግ፡ እንደልጇ ዕርገት በአርባኛው ዕለት፡ ወደሰማይ ያረገችባት መስከረም ፳፩ ቀን እሑድ ናት።

"ቶማስም፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታውኮበት፡ 'ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቼ ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ። አኹን ደግሞ፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ይኸው፡ የአንቺን የፍልሰት ትንሣኤ፡ ቀድመውኝ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ!' ብሎ፡ ማዘኑን ገለጠላት።

"ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ 'አይዞህ! አትዘን! እኒያ ወንድሞችህ፡ በልጄ ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የእርሱን የትንሣኤ ምሥራች፡ ከሌሎች ሴቶች ሐዋርያት ሰምተው ሳያምኑ በመቅረታቸው፡ ኋላ፡ ከአንተ በፊት፡ እነርሱ ያዩት ቢኾንም፥ አንተ፡ ለጊዜው፡ በዚያ ባለመኖርህ፡ ሳታየው ብትቀርም፡ ዕርገቱን፡ ዐብረሃቸው ኾነህ አይተሃል። አኹንም፡ እነርሱ፡ የእኔን፡ የፍልሰት ትንሣኤዬን ያዩ ኾነው፡ አንተ፡ ያላየህ ብትኾንም፡ ይኸው፡ አኹን ደግሞ፡ ዕርገቴን ያየህ፡ አንተ ብቻ እንጂ፡ እነርሱ አላዩም። ስለዚህ፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ በበለጠ የታደልህ፡ አንተ ነህ፤ ፍልሰቴንም፣ ዕርገቴንም፡ ኹለቱንም፡ በአንድነት አይተሃልና።' ብላ አጽናናችው። ቀጥላም፡ እንዲህ አለችው፡- 'አኹንም፡ ወደእነርሱ ኺደህ፡ ‹ዐረገች!› ብለህ፡ ንገራቸው።' ይህንም ብላ፡ የውስጥ መጐናጸፊያዋን ሰጥታ፡ ሰደደችው። እርሱም፡ በግንባሩ ሰግዶና በእጇ ተባርኮ ተሰናበታት።

ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባዔና በጉባኤ የሰነበቱ ወንድሞቹን ሐዋርያትን ሲገናኛቸው፡ "እረ! የእመቤታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፡ የኾነውን ኹሉ፡ ነገሩንም፡ አንድ በአንድ እየተቀባበሉ፡ ምንም ሳያስቀሩ ነገሩት።

እርሱም፡ ነገራቸውን፡ ካስጨረሳቸው በኋላ፡ "ታዲያ! አኹን፡ ቅድስት እናታችን፡ የት ነው ያለችው? እጅግ ናፍቃኛለችና፡ ኼጄ፡ እንድሳለማት፣ እንድሰግድላትም፡ ያለችበትን መካን አሳውቁኝ!" አላቸው።

በዚህ ጊዜ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፥ ዐብረውት ያሉት፡ የቀሩት ሐዋርያትም፡ ኹሉም፡ የሚመልሱት አጥተው፥ አቀርቅረው፡ ዝም አሉ።

ቶማስም፡ ጥያቄውን በመቀጠል፡ "እንዳበሠራችሁኝ፥ በትንሣኤ መልክ ከታየችበት፡ ከመጀመሪያው አስተርእዮቷ በኋላ፡ እስካኹን እንዳስለመደቻችሁ፥ ልጁ መሲሐችንም፡ እስከዕርገቱ ድረስ፡ ዐልፎ ዐልፎ እየተገለጠ ያነጋግረን እንደነበረው ኹሉ፡ ምናልባት፡ ድንገት፡ በመካከላችን፡ ትገኝ እንደኾነ፡ እንጠብቃት ይኾን?" አላቸው፡ እያንዳንዳቸውን፡ ተዘዋውሮ እየተመለከተ።

እነርሱም፡ ኹሉም ማለት ይቻላል፡ "አዎን! ልክ ነህ። ይህ ያልከው ነገር፡ 'አይኾንም!' አይባልም። እንዳልኸው፡ ምናልባት፡ ሊኾን ይችል ይኾናል!" በሚል ስሜት ይመስላል፡ ቀና ብለው እያዩት፡ ወደዝምታቸው ተመለሱ።

በዚህን ጊዜ፡ ቶማስ፡ ባጭር ቃል፡ "መቼም፡ 'አታምኑኝም!' ብዬ ነው እንጂ፡ ደስ ይበላችሁ! ቅድስት እናታችን ዐርጋለች! በልጁ ጊዜ፡ በራሴ ድክመትና ጥፋት፡ በራሴ ላይ ያሳደርሁትን፡ የዘለዓለም የፀፀት እሳት፡ በርኅራኄዋና በቸርነቷ ልታስወግድልኝ ፈቃዷ ኾኖ፥ ለዚያ በደሌ፡ ዋጋዬን እኔ መክፈል ሲገባኝ፡ እንዲያውም፡ ይህ ካሣ ይኹንህ!' ብላ፡ ይህን ቸርነት አደረገችልኝ! በማለት፡ ወንድሞቹ ሐዋርያት ትኩር ብለው እየተመለከቱት፡ በግንባሩ ተደፍቶ፡ ሥቅሥቅ ብሎ አለቀሰ፤ የደስታ እንባውንም አፈሰሰ።

ሐዋርያትም፡ ባንድነት ኾነው፡ ከወደቀበት ካነሡት በኋላ፡ "እንኳን ደስ አለህ!" ከሚል ቃል ጋር በፍቅር አጽናኑት።

ቶማስም፡ በደስታ ፈክቶ፡ "እኔ በሌለሁበት ስለኾነው ኹሉ፡ እናንተ፡ አኹን ያላችሁኝን ጨምሮ፡ ከእርሷ ሰምቼዋለሁ። ለኹላችንም የሚኾን የእናትነት ምክሯንም ለግሣኛለች። በብዙ አጽናንታኛለች። ይህን የውስጥ ተደራቢ መጐናፀፊያዋን፡ ለኹላችንም፡ ለበረከት እንዲኾነን፡ በእኔ እጅ ሰድዳላችኋለችና፡ ተረከቡኝ!" ብሎ ሰጣቸው።

ሐዋርያትም፡ ያን፡ የእናትነት ስጦታዋን በማየታቸውና በማግኘታቸው፡ እጅግ ደስ ብሏቸው ተቀብለው፡ ለበረከት ተካፈሉት።

ይህ በኾነ፡ ልክ በዓመቱ፡ የቀሩት ሐዋርያት፡ "ቶማስ፡ ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተሽ አሳዪን!" ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛውን፡ የ፪ ሳምንት ሱባዔያቸውን፡ ቶማስ ጭምር፡ ዐብሮአቸው በተገኘበት፡ በነሐሴ ፩ ቀን፡ በተገቢው ጾምና ጸሎት፥ ትህርምትና ብሕትውና፡ በአንድነት ጀመሩ።

የኹለተኛው ሳምንት ሱባዔ፡ በነሐሴ ፲፬ ቀን፡ ከተፈጸመ በኋላ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፡ ሐዋርያት ያደረጉት ይህ ነው፦

በመጀመርያ፡ ከእየግል በአታቸው ወጥተው፥ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቷና በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፤ በኪዳነ ምሕረትነቷም፡ ኹሉን አንድ አድርጋ በምትመለከውና በምታስመልከው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ዙሪያ፡ በአንድነት ተሰብስበው፡ ሱባዔያቸውን፡ በሰላምና በፍቅር ስላስፈጸመቻቸው፡ ምስጋናቸውን፡ በኅብረት ጸሎታቸው ውዳሴና ቅዳሴ አቀረቡ።

በመጨረሻ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ የሚከበረው በዓል፡ ፍልሰታን በሚመለከት፡ እስካኹን የተነገረውን ኹሉ፡ የሚያካትት ኾኖ፡ ፍጻሜው፡ በሰማያት ኾነ በምድር ዓለማት፥ በሥጋዊዉ ኾነ በመንፈሳዊው ፍጥረት ዘንድ፡ ምን እንደኾነ፥ ከምን ዓይነቱ የብቅዓት ደረጃም እንደደረሰ፡ አረጋግጦ የሚያሳየውን መለኮታዊና ፍጥረታዊ ክንውን፡ መመልከት ነው።

ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ የመጨረሻ አጭር የማጠቃለያ ቃል ይገልጸዋል፡- በነሓሴ ፲፮ ቀን በሚውለው፡ በፍልሰታ ለማርያም መታሰቢያ ዕለት፡

ሓዋርያትና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ወደሰማያዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው ኼደው፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመንበረ ጸባዖትነቷና በቅዱሱ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያነቷ የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና አዩ! ያያሉም።

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ እርሷን፡ ቅድስት እናቱን፡ መንበር፥ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ካህን፥ ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፥ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን፤ ፊልጶስንም፡ ንፍቅ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፥ ራሱም ቆርቦ፥ እናቱንም አቍርቦ፥ ካህናቱንና ሓዋርያትን፤ እነርሱን የመሰሉትንና በዚያ የታደሙትን አማኞቹን ኹሉ አቆረበ። ያቆርባልም።

በዚያን ጊዜ፡ በመላው ፍጥረታተ ዓለማት ዘንድ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ታላቅ ደስታ፥ ታላቅ ሓሤት ኾነ! ይኾናልም።

(ራእ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፪፥ ፩-፲፯።)

\+ + +